የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር - ዴሞክራሲያዊ ምትሕብባር ትግራይ
TIGRIAN ALLIANCE FOR NATIONAL DEMOCRACY (TAND)
e-mail: czanareg@hotmail.com

# ሃገር ቤት ስለ መግባት ወቅታዊ መግለጫ
# የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር (ት.ዴ.ት./TAND)

ኢትዮጵያ ላለፉት 27 ዓመታት በህወሓት/ኢህኣዴግ መዳፍ ስር ወድቃ፣ ህዝቡ የብዝበዛና የኣፈና ሰለባ ሆኖ ሲማቅቅ እንደኖረ ዓለምየተገነዘበውሓቅ ነው። ይህ እውነታ የወለደውብሶት ህዝቡን ለኣመጽ ከማነሳሳት ኣልፎ ኢህኣዴግ እንዲናጋና ከውስጡምኣዲስ የለውጥኣራማጅ ሓይል እንዲፈጠር አስገድዷል። ይህ በዶ/ር ኣብይ ኣህመድና በኣቶ ለማመገርሳ የተመራው የለውጥኣራማጅ ሓይል ይዋል-ይደር ሳይል ኢትዮጵያን የዴሞክራሲ ፈር አስይዞ፣ ከመከፋፈል ወደ አንድነት፣ ከኣፈና ወደ ነጻነት ትሸጋገር ዘንድ ታሪካዊ አስተዋጸኦ በማድረግ ላይ ይገኛል። ይህ ሓይል ሂደቱ እግቡ ለማድረስ ምበጠ/ሚኣብይ የሚመራ ኣዲስ መንግስት ማስረቶ የለውጡን ጎዳና ተያይዞታል።

ይህ ህዝቡ የተዋደቀለት የለውጥሂደት እንዲሳካና ህዝቡ የተመኘውፍትሃዊ ስርዓት እውን እንዲሆን ማንምሰላም፣ እኩልነት፣ አንድነትና እድገት ፈላጊ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ያለማቋረጥ ሊደግፈውና ሊዋደቅለትምይገባል። ማንጠልን በመቃወም፣ አንድነትን በማራመድ ከ30 ዓመታት በፊት ከህወሓት ተለይቶና ለ 23 ዓመታት በስደት ላይ ሆኖ ሲታገል የቆየውት.ዴ.ት./TANDም፣ በዚህ የለውጥ ጎዳና እንደሚሰለፍ ከውጥኑ ጀምሮ በመደጋገም ግልጽ ኣድርገዋል። በሚልዮኖች የሚቆጠር የኣዲስ ኣበባ ህዝብ ቅዳሜ አደባባይ ወጥቶ ያሳየውን የድጋፍ ሰልፍምበማሉ ልብ ኣድንቋል። ይህንን ታላቅ እርምጃ ለማደናቀፍ ሙከራ ያደረጉ ሽብርተኞችንምአምርሮ እያወገዘ ጉዳት ለደረሰባቸውወገኖቻችንም ጽናቱን ይመኝላቸዋል።

እየተከሰተ ያለውየህዝብእንቅስቃሴ የሚጨውፍትሃዊ ስርዓት አመላካች ነጸብራቅ ሆኖ እያለ፣ በሌላ በኩል ግን የድሮዎቹ የህወሓት/ኢህኣዴግ ባለስልጣናት ጥቅማቸውንና ስልጣናቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ የለውጥሂደቱን ለማደናቀፍ ልዩ ልዩ ማሰሪ ዘዴዎች በማጠንጠንና ብሎምበመቃወምላይ እንደሚገኙ ግልጽ እየሆነ መጥቷል። ይህ ዓይነቱ የሃገርንና የህዝብን ብሩህ ተስፋ ወደ ጎን የሚገፈትር ጨለምተኛ እንቅስቃሴ ሁሉ ት.ዴ.ት./TAND ኣሁንም አምርሮ ይቃወማል።

የ ት.ዴ.ት./TAND ማእከላይ ኮሚቴ እነ ዚህ ከላይ የተጠቀሱትን ሁለቱ ተጻራሪ ክስተቶችና ባጠቃላይ በለውጡሂደት ላይ ማከል ያለበትን ኣስተዋጾኦ የሟ መግምኣስቸኳይ ስብሰባ ከ 22 – 23 / 06 / 2018 በማካሄድ የሚከተሉትን ውሳኔዎች ኣስተላልፏል።

1ኛ. ት.ዴ.ት./TAND በሃገራችን እየተካሄደ ያለውን የለውጥሂደት በሚደገፍ ሙሉ ሃይሉን ሃገር ቤት ውስጥኣስገብቶ የበኩሉን ኣስተዋጾኦ ለማበርከት ድምዳሜላይ ደርሷል።

2ኛ. ት.ዴ.ት./TAND ሀ/የ ኢትዮጵያ ህዝብየጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ) ማሕራች ኣባል ድርጅት ሆኖ የህብረቱን ዓላማከግቡ ለሚድረስ ኣሁንምተሳትፎውን የሚቀጥል ሚሆኑን ኣጽንኦት በማስጠትና፣ ለ/እንደዚሁምለውጡን ፈላጊ ከሆኑ የተለያዩ የትግራይ ሲቪል ንቅናቄዎች ጋር ያለውን ኣጋርነት በትጋት እንደሟፋበት በሚረጋገጥ፣ ኣሁን በሃገራችን ውስጥየተጀሚረውየለውጥ ሂደት ሳይደናቀፍ ይቀጥል ዘንድ ት.ዴ.ት./TAND የበኩሉን ኣስተዋጾኦ ማበርከት ይቻላል ብሎስለኣማ ባስቸኳይ ሃገር ቤት ለመግባት ወስኗል።

3ኛ. ይህ ውሳኔ በተግባር ላይ ይውል ዘንድኣስፈላጊ ሁኔታዎችን ለማምቻቸትና ከለውጥኣራማጆቹ ጋር ተቀራርቦ ለመመካከር በኣፋጣኝ አስፈላጊ እርምጃዎችን እንዲወስድ ውሳኔ ኣስተላልፏል።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!

26.06.2018